# ፊሽካው ተነፋ!የትኛውፊሽካ?.

ደራሲ ወዲ አፈወርቂ

መሪ ተዋናይ ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ እንደ ኮማንደር

አርበኛ ዘምነ ካሤ እንደ ጦር ሜዳ

ቃል አቀባይ

መሣይ መኮነን እንደ ዜና አቅራቢ

ቦታ ወልቃይት አንዲ ትግራይ

አንዲ ጎንደር

ከዘላለም ሽፈራው

በተወለድኩበትና ባደኩበት አካባቤ ወልቃይት ጠገዴ ፊሽካው ተነፋ (ነፋ)ሲባል ሁለት ትርጉም አለው። አንደኛው ፊሽካው ተነፋ ሲባል ለአንድ ተልእኮ ፤ሥራና ግዳጅ የመጠንቀቅ፣የመዘጋጀት፤ የመጀመርና የመጨረስ ምልክት ነው። ሌላው ትርጉም ፊሽካውን ነፋ ወይም ተነፋ ማለት ውሸቱን ጀመረ፣ መቀደድ ጀመረ፣ የሀሰትና የፈጠራ ወሪውን ነፋ አስተጋባ ማለት ነው።

ሰሞኑን በኮማንደር ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ የሚመራው የአርበኞች ግንቦት ሰባት ኃይል በወልቃይት ና ትግራይ ግዛት ወታደራዊ ጥቃት አድርሶ ሀምሳ የወያኔ መከላከያ አባላትን ገለው ከስልሣ በላይ አቁስለው አካባቤውን ተቆጣጥረው ግንባሩ ወደ ጎንደር እየገሰገሰ ስለ መሆኑ በእሳት ራዲዩና ተሌብጅን በሰበር ዜና በድምፃዊ መረዋው በጋዜጠኛ መሳይ መኮነን እቅራቢነት ተነግሮናል። በተከታታይ ቀናት ጦርነቱ እንደቀጠለ በመግለፅ ቀላል የማይባል የወያኔ ጦር በአርበኞች ግንባር እንደመከነና እንደተገደለ በመግለፅ የግንባሩ ቃል አቀባይ አርበኛ ዘመነ ካሤ እንዳሉት ይጠበቅ የነበረው ጦርነት ተጀምሮአል ማለት ፊሽካው ተነፍቶአል ከዚህ በኃላ በውጭና በውስጥ ያላችሁ ሀገር ወዳድ ኢትዪጵያውያን ተቀላቀሉን ሲሉ ጥሪ አድርገዋል ። የነጋሪቱ ወሪ እንደ ተበሰረ ና እንደተጎሰመ ኮማንደሩም ሸሚዛቸውን ጠቅልለው በሚሪላንድ ግዛት በዩንበርሲቴ ፓርክ ኢትዪጵያውያን በሚከብሩት የእግር ኮስ ስትዲዩም የወታደር ኮፍያ አድርገው በብሔር ብሔረሰቦች ተከበው በድል አድራጊነትና በአሸናፊነት ስሜት ሲንጎራደዱ ታይትዋል።

ዜናው በዚህ ግፈኛና ከፋፋይ አገርና ትውልድ አጥፊ የሆነ የህዋት አምባገነን መንግሥትን የመውደቅ ጉጉትና ናፍቆት ላለው ኢትዪጵያዊ ዜናውን ከላይ ሲዩት ያስደስታል ነገር ግን ጦርነት ተካሄደበት የተባለበትን ቦታ ለሚውቅ፣ አካባቢው ከኤርትራና ከሱዳን ድንበር ግንኙነት አንፃር ወያኔ ህዋት ከፍተኛ የጦር ኃይል ያለው በዚሁ ክልል መሆኑን ለተረዳ በማንከደው ጉዳይ የአካባቢውና የምስራቅ አፍሪካ የፀጥታ ጠባቂ የምእራብያውያን በተለይ የዩናይትድ ስቲት ሸርካ በሚል ከግብፅና ከደቡብ አፍሪካ ጭምር

ባልተናነሰ ምእራብውያን ና አሜሪካውያን በዘመናዊ የጦር መሳሪያ ያስታጠቁትና ሁለገብ ወታደራዊ ሥልጠና የሰጡት ቢኖር ይህውን ድርጅት ህዋትን ነው። የህዋት ዋናው ቤዝ ደግሞ ይህው.

ትግራይ ክልል ነው። ህዋት የወልቃይት፤ጠገዴንና አብደራፊን በኃይልና በጉልበት ከጎንደር ግዛት ነጥለውበትግራይ ክልል ከአደረጉትበኃላ አካባቢው የወታደር ቀጠና እድኪመስል ድረስ ከፍተኛ የመከላከያ ሠራዊት ያለበት ክልል ነው። ሰለዚህ ደፋሩ የአርበኞች ግንቦት ሰባት ኃይል ከኤርትራ ተነስቼ በክረምቱ ተከዜን ተሻግሪ በዚህ ቀጠና ነው ጥቃት ሰንዝሪ የህዋትን ሠራዊት ደምስሸ ድል አደረኩህ በማለት ያበሰረው ትግራይ ገብቼ የጦርነት ትርኢት አሳየሁበት ያለን። ግንቦት ሰባት ይህን ታሪክ እንዴት ፈጠረው?

እውነተኛው ነገር ሳንጃ፣ዳንሻ፤ ላይና ታች አርማጭሆ፣ማይ ፀብሪና አዳርቃይ የአካባቤው ህዝብ በጎበዝ አለቃ እየተመራየሚደርጋቸው ውጊያዎችና አመፆች አሉ ።ይህ ግን በፍፁም ከግንቦት ሰባትና ከኤርትራ ጋር አንዳችም ግንኙነት የለውም። በዚህ ንቅናቄ ተሳትፎ ያላቸው መሪዎች አባቶቻቸውና የሥጋ ዘመዶቻቸውች በወያኔና ሻቢያ

የተገደሉና ሰለባ የሆኑ የእውነትና የቆረጡ ጎንደሪዎችናቸው። ይህ ንቅናቂ የቆየ ነው። እነዚህን ብረት ያነሱ ወገኖች የማያውቅ የለም።

ወያኔ ሥልጣን ከመያዙ በፊትና በኃላ ከፋኝ በሚል ሲንቀሣቀሱ ከቆዩ በኃላ አንዲ ሲጠናከሩ አንዲ ሲዳከሙ ባለፍት.

አስር ዓመታት ጠንከር ብለው እየተንቀሳቀሱ ያሉ ናቸው። ባለፈው ሳምንት እነዚህ ኃይሎች ከሱዳን እንደ ተለመደው በኮንትሮባንድ የመሣሪያ ግዥ አድርገው ወደ ወልቃይት ሲገቡ ከወያኔ ታጣቂ ኃይሎች ጋር የከፋ ውጊያ አድርገዋል። በውጊው ቀላል የማይባል ህይወት በሁለቱም ኃይሎች ሙተዋል። የውጊያው ዜና በጎረቤት ሀገር ኤርትራና ሱዳን እንዲሁም እድሜ ለቴክኖለጅ በቴሌፎን ወዲያውኑ ጀርመን ፤ካናዳና አሜሪካ ያለን ተወላጆች እሳት ዜና ብሎ ታሪኩን

በርዞ ከማቅራቡ በፊት እኛ ሰምተነዋል። ይህ ግጭት ሲካሄድ  እንኮን ሠራዊት ወፍ ከኤርትራ አልበረረም ወይም አልነበረም ።ግጭቱ ሲካሄድ የአርበኞች ግንቦት ሰባት የውጊያው ቃል አቀባይ ዘመነ ካሤ ኤርትራ ነበር የነበረ የግንባሩ ኮማንደር ደግሞ ሜርላንድ ነው የነበሩት። እነ ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ ና የእሳት ረዲዩና ቴሌብጅን የተሳሳቱት በሁለት ነገር ነው አንደኛ ባለፈው አርባ ዓመት ወልቃይትጠገዴናአርማጭሆ የጦርነት ቀጠና ሰለነበር  ሁሉም ድርጅቶች ነፍጥ ያነሱበት፣ ውጊያና የጦርነት ቤዛቸው ስለነበር በዚሁ ጦርነት የተስደድና አሁን በሰሜን አሜሪካ፣ አውሮፓና ካናዳ የምንኖር ተወላጆች እንደምንኖር የአካባቢችን ሁኔታ በየጊዜው እንደምንከታተል ግምት አልሰጡትም ወይም ንቀውታል። በእነርሱ ግምት ወልቃይት ጠገዴ ሲባል እንደ ሩቅ ምስራቅ አፍሪቃ ወይም ኢሽያ የመንደር ወሪ ዜናው ተሰምቶ የሚታመን አድርገውታል።

ሁለተኛው በዚህ የፈጠራ ወሪ ውጭ ያለውን ህዝብ በመጀንጀን ከሚደረገው የገንዘብ ማሰባሰብ ይልቅ እውነቱንና መሪት ላይ ያለውን
የሚውቀው ህዝብ ነገ ምን ይለናል ብለው ለህዝብ ግንዛቤ፣እውቀትና
ትዝብት ከበሪታ አልሰጡም ይህም እውነታው ሲወጣ !ድርጅትንና አባሎችን የሚዋርድ ነው

የወልቃይት ጠገዴና የጠለምት ታጣቂዎች በወያኔ ላይ ነፍጥ ያነሱ ኃይሎች ዛሪ ከወያኔ ጋር ይዋደቁ እንጅ ትናንት ሻቢያ በእነርሱ፣ በኢትዩጵያ ሠራዊት ላይና በህዝቡ ላይ የፈፀመውን በደል በፍፅም አይረሱትም እንደ ኤርትራ መንግሥት ና ሻቢያ ለኢትዩጵያና
ህዝብና ሉአላዊነት ክፉ እምነት ያለው የለም። ስለዚህ የነዚህን ጀግኖችና አርበኞች ተጋድሎ ከሻቢያና
ምንጭንናወታደራዊ መሰረቱን
ኤርትራ ካደረገ ቡድን ጋር ለማያያዝ መሞከሩ ታሪካዊ ውንብድና ከመሆኑ በላይ የተወላጅን ጦርነት የአርበኞች ግንቦት ሰባት ሥራ አድርጎ ማቅረብ እሳዛኝ ነው ።

በዚህ አጋጣሚ  ለክቡር ዶ/ር ብርሀኑ የምመክራቸው ሳይሆን የምነግራቸው ሀገር በፕሮፕጋንዳ ሥራ ብቻ ነፃ አይወጣም። ፕሮፕጋንዳ መሪት ላይ ካለው ሥራ ጋር ካልተዋሀደ ውሸታም ፣ቱሪ ናፋ ፣ ፍሽካውን ነፋ ፣ ጥሩምባውን ነፋ ያሰኛል ይህ ስም ደግሞ ከተደጋገመ  ለእርሰዎ፣ለድርጅተዎና ነፃነት ፈላጊ ለሆነው አባልዎ ጥሩ አይሆንም ።ሌላው በሰሜን ጎንደር ኃይል ይዞ ለመንቀሣቀስ
አልፎ ለመሄድ ሁለት መሠረታዊ ጉዳይ ያስፈልገወታል አንደኛው ኢትዩጵያዊነትን ያስቀደሙ መሆንዎ ሁለተኛ የአካባቢውን ህዝብ ያመኑ፣ ያከበሩ ና ያወቁ ሲሆን ብቻ ነው። በእኔ እምነት ሁለቱንም አያሞሉም ድርጅትዎ ግንቦት ሰባት የተቀመረውና የተደራጀው ኤርትራ ያሉ ከኢትዩጵያ ነፃነትን ተቀዳጅተን የየራሳችን መንግሥት እንገነባለን ከሚሉ ነፃ አውጭ ድርጅቶች የእነርሱን አባላት መሰረት
አድርጎ ኢትዩጵያውነትን  በሽፋንነት በመጠቀም ኢትዩጵያውያን ድርጅቶችን በማኩሰምናበማጥፋት፣ እንዲሁም ኢትዩጵያዊነትን የሚቀነቅኑ ዜጎችንናታጋዩችን አንገት ለማስደፋት ተሳዳቢ፤ተናዳፊና ጋጠ ወጥ የሆኑ ኢትዩጵያዊነትን የሚጠሉ የነፃ አውጭ ድርጅቶች ጥምር ድርጅት ቢኖር ግንቦት ሰባት ነው ይህ ማለት ነፃነት ፈላጊ ኢትዮጵያን የሉም ማለት አይደለም ቢኖርም በቁጥራቸው አናሳና ግንቦት ሰባት ምን እያደረገ ስለ መሆኑ ግንዛቤ ያልወሰድ ወይም በረጅሙና አሰልቺው የዲሞክራሲ ትግል የውስጠ ፓርቲ ትግል አሰልችቶቸው እንዲሁ ያሉ ነው የሚሄኑት። ስለዚህ ግንቦት ሰባት ኢትዩጵያን ለነፃነትና ለአንድነቶ ይቆማል ታግሎ ለድል ያበቃታል የሚል
የለም። ከዚሁ ጋር ታያይዞ ግንቦት ሰባት አማራውን ነፍጠኛ ነው ብሎ የሚምን ድርጅት ነው ለዚህም ከሌሎች ነፃ አውጭ ድርጅቶች ጋር ሲሰራ በኢትዩጵያዊነቱ ከሚምነው ከአማራ ድርጅት ጋር መስራት አይፈልግም ልክ እንደ ሞረሽ ወገኔ የአማራ ድርጅት አይነት ። ሞረሽ የመገንጠልና የነፃነት ጥያቄ ቢኖረው ንሮ ግንቦት ሰባትም ሆነ እሳት ወዳጅ ያደርጉት ነበር። ሌላው ግንቦት ሰባት ለሀገር ድንበር
ለዜጎቹና በተለይ ለአማራው ዜጋ ደንታ እንደለለው የሚሳየው የህዝባዊ ወያኔ ሀርነት መንግስት በሱዳን ድንበር 1600ኪሎ ሚትር ለም መሪት አሳልፎ ለሱዳን መንግሥት በውለታ ሲስረክብ ይህ ጉዳይ ያሳሰባቸው ሀገር ወዳድ ኢትዩጵያውያን የድንበር ኮምቴ በማለት አቆቁመው የጉዳዩን አሳሳቢነትና አባቶቻችን ደም ገብረው አጥንት ከስክሰው ያቆዩትን ድንበር ህዝባዊ አመኔታና ሀገራዊ ኃላፊነት በማይሰማው መንግሥት የተፋፀመ ስለሆነ ይህን ህገ ወጥና ታራካዊ መረጃ የለለው ከኢትዩጵያ ህዝብ ጀርባ የተሰራ ክህደትና ሤራ እናወግዛለን አሁንም ሆነ ለወደፊት ትውልድ ይህን የታሪክ ጠባሳ ጥሎ ማለፍ አይገባም በሚል ለተባበሩት መንግስታት፣ ለአፍሪካ ዩንየን፣ ለሱዳን ፕሪዘርዳት፣ ለአውሮፖ ዩኒየን ፅህፈት ቤትና ለስቴት ዲፓርትመንት በአጠቃላይ ከሀያ በላይ ለሆኑ ድርጅቶች ደብዳቤ በተፃፈበት ሰአት ደብዳቤውን ክብደት ለመስጠት የተለያዩ ኢትዩጵያውያን የተቃዋሚ ድርጅቶች ፣ የሲፒክ ድርጅቶች ፣ የኃይማኖት ተቆማት ፊርማ እንዲስቀምጡ ተጋብዘው  ሁሉም ሲፈርሙ የዶ/ር ብርሀኑ ነጋ ድርጅት ግንቦት ሰባት ድርጅትናከእርሰዎ ጋር የሚሰሩት የነፃ አውጭ ድርጅቶች አንፈርምም ያላችሁት ።ይህን እኛ  ኢትዮጵያውያን ፣ እኛ ጎንደሪዎች፣እኛ

መተማዎች ወልቃቶች፣ጠገዴዎች፣ጠለምቶችና አርማጭሆዎች እናውቃለን ዶ/ ር
ብርሀኑ ጦርነቱን እንዳካሄድላቸውና እንዲሞትላቸው የሚፋልጉት ይህን ህዝብ ነው ያውም ባልዋሉበት ሜዳ የእኔ ሠራዊት ተዋጋ አሉን

ክብር ዶ/ር ብርሀኑ እርሰዎኮ ጎንደሪውንና አክትብሲቱን የሚፈልጉትና መድረክ የሚሰጡት ለልመና ሲሆን ብቻ ነው። በተረፈ ከሥራ አመራርዎ ጀምሮ በየቦታው ያለዎት የሰየሞቻው የቻብተር አመራረዎት በቀጥታ ይሁን በተዘዋዋሪ ከኢትዬጵያ ነፃነትን እንፈልጋለን የሚሉ የነፃ አውጭ ድርጅቶች ተወካዮች ናቸው።

ቀደም ብየ እንደገለፅኩት ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ እየሰሩት ያለው ሙሉ ግዜቸውን መስዋእት በማድረግ ነገ ነፃ መንግሥት እንገነባለን በሚል በህልም ፈረስ ከሚጋልቡ ዘጠኝ ነፃ አውጭ ድርጅት

በህልም ፈረስ ከሚጋልቡ ከዘጠኝ ነፃ አውጭ ድርጅችና አባላትና
ከሻቢያ ጋር ጭምር ነው። እነዚህ ቡድኖች ኢትዬጵያውያኑን ኃይል ለማዳከም በመካከለኛ ፕሮግራም በአንድ ድርጅት ማለት በግንቦት ሰባት ድርጅት ስም በመሆን የፕሮፕጋንዳና የሳይበር ጦርነት እያካሄድ ነው።እነዚህ ኃይሎች ሙሉ ጊዜቸውና ጉልበታቸውን ስለሚጠቀሙ ትልቅ ጉልበት ያላቸው ይመስላሉ። ዓላማቸው አንድና አንድ ነው ሻቢያ ና ኢሳያስ አፈወርቂን በኢትዬጵያውያን ስነ ልቦናዊ ተቀባይነት እንዲኖረው በማድረግ ኢትዬጵያዊ ኃይልና ኢትዬጵያን በማዳከምና በማፈራረስ ሀገራችንን ከዘጠኝ ቦታ በመከፋፈል ኤርትራ በምስራቅ አፍሪካ ታላቅና ተፅእኖ ፈጣሪ አገር ለማድረግ እየተሰራ ነው ለዚህም የኤርትራ መንግስት ትልቅ ገንዘብና የሰው ኃይል መድቦል ።

በመጨረሻ ለግንቦት ሰባት መሪ ለዶ/ር ብርሀኑ ነጋ የምገልፅላቸው በፕሮፕጋንዳና በጨበጣ ትግል የተታረመሰ እንጅ ነፃ የወጣ ሀገር የለም። እርሰዎ አሁን የሚከተሉት አካሄድ ኢትዬጵያን የሚድናት ሳይሆን የሚጠፋት ነው የእርሰዎ ችግር ትጉሉን ሲጀምሩ በለለ ኃይል
ጣራ አደረሱትና መሪት ላይ ካለው እውነት አልያያዝ አለዎት ይባስ ብለው ከጊዜ ወደ ጊዜ በፕሮፕጋንዳ በማጦዘወት የሚሸሹበትና የሚጠጉበት እንዳጡ የተረዳው ሻቢያ ለአሽከርና ለሎሌነት መደብዎ እርሰዎ ተንበርክከው ተከታይዎችን አሳፍረው ጭራሽ የኢትዬጵያ ህዝብ እንዲነነብስ ይፈልጋሉ ።

ፅሑፊን ማጠቃለያ ከመስጠቴ በፊት የምለው መነሻየ ከኤርትራ ተነስቶ በወልቃይት ጠገዴ ላይ ወታደራዊ ጥቃት አድርሻለሁ ያለው አርበኞች ግንቦት ሰባት በእሳት ያቀረበው ሰበር ዜና ውሸትና ቱሪ ናፋ መሆኑን አረጋግጨ ለወገኖቸና ለኢትዬጵያውያን ለማሳወቅ
ይህን ለመፃፍ ስነሳ ስሜቴ ተነክቶ ስለ ግንቦት ሰባት ምንነት ለመዳሰስ ሞክሪለሁ።ኤርትራ አሁንም ነፃ አልወጣሁም ነፃነቴ የሚረጋገጠው ኢትዬጵያ የምትባል ሀገር ስትፈርስ ነው በሚል
እየሠራ ነው።ለዚህም ከዘጠኝ ነፃ አውጭ ድርጅትና የነዚህ ቅይጥ የሆነው ግንቦት ሰባት ህዝቡንና የተቃውሞን ጎራ ከፋፍሎ የሻቢይ፣የኦነግ፣የአፋር፤ የኦጋዴን፣ የቤንሻንጉል ወዘት አማርኛ ተናጋሪዎች በመጠቀምና በማስጮህ ሻቢያ የበጠበጠልን መርዝ አይናችን ጨፍነን እንድንጠጣላቸው ይፈልጋሉ ትኩረታችን ኃይላችንና ጉልበታችን በህዋት ወያኔ እንዳይሆን ሻቢያ ና ግንቦት ሰባት አዲስ ሥራ ሰጥተውናል። በመጨረሻ ለክቡር ኮማንደር ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ ስለ ጎንደር የሚናገራቸው ጎንደሪ የውሸትና አጭበርባሪ መሪ አይወድም አንድን መሪ ወይም ድርጅት ውሸታምና አጭበርባሪ ነው ብሎ ካመነ ልቡን እንደ ገና ለማግኘት ከባድ ነው። በእኔም ግምት ፐረፐጋንዳ የሚጠቅመው መሪት ላይ እውነት ብዙም ባልተጋነነመልኩ ሲቀርብ ብቻ ነው።በአንድ ጦር ሜዳ በተደረገ ውጊያ አንድ ድርጅት ማሸነፍን ካረጋገጠ በኃላ በሚስተላልፈው ዜና አንድ መቶ ገድሎ ሁለት መቶ ገደልኩ ቢል ሃምሳ አቁስሎ አንድ መቶ አርባ አቆስልኩ ቢል ና መሣሪያም ማረከህ ቢል ጥሩ ፐረፐጋንዳ ነው
ነገር ግን እንደ ሰሞኑን የግንቦት ሰባት ፐረፐጋንዳ ባልዋልበት ጦር ሜዳና ጦርነት ቦታና ጊዜ ጠቅሶ ይህን ያህል ገደልኩ ይህን ያህል አቆሰልኩ የሚል ነጭ ወሪ ለጎንደሪ አይመችም ።ሌላው የምመክረዎት የሀገሩን በሬ በሀገሩ የሚል ተረት አለ ጎንደሪ ተጠራጣሪ ነው እንኮን አብሮ ለመዋጋትአብሮ ለሙብላትም
ጠይቆና መርምሮ ነው አብሮ የሚቀመጥ የቀደምት ጀግኖች
አባቶቹ እንደዛ ብለው ነው ሀገሩንና ድንበሩን ኃይማኖትን የጠበቁለት
ፍታውሪ መስፍን ረዳ፣እነ አባይ ወልደ ማርያም፣እነ አዳነ መኮነን፣እነ
መኮነን ነጋሽ፣እነ ብሪ ዘገየ፣እነ በዛብህ አለሜ፣እነ አየለ ተሰማ፣እነ
አሞራው ውብነህ ተሰማ እረ ስንቱ በግንባር ተዋግተውና አዋግተው ነው ያችን ሀገር ነፃነቶን ጠብቀው ለእኛ ያቆዩን።
ወልቃይት ጠገዴ ጠለምት አርማጭሆ ወገራ ዳባት ደባርቅ ጭልጋ ጫቆ አዳኝ አገር ነፋስ መውጫ ፍሽካው ከተነፋ ቆይቶል የማይቀረው የነፃነት ድል ለኢትዬጵያውያን የሚስተገባውም እዚህ ቦታ ነው ይህን ለማድረግ የጎንደር ህዝብ የሻቢያና የነፃ አውጭ ድርጅቶችን ይሁንታ አያስፈልገውም።

በመጨረሻ ያለኝ መልእክት ለወልቃይት ጠለምትናጠገዴ ማህበርና ለጎንደር ህብረት ማህበር ነው። ላለፍት አርባ አመታት ጎንደር በተለይ ሰሜን ጎንደር የጦር አውድማ በመሆን በህገሩና በትውልድ ላይ ያስከተለው ቀውስ እንዲህ ቀላል አልነበረም። ነፃ እናወጣሀለሁ ያሉት ድርጅቶች የከፋ ጊዜ ሲመጣ ጥለውት በመሸሽ ለደርግና ለወያኔ ጨካኞች አሳልፎ በመስጠት በደርግ ጊዜ በአውሮፕላን መርዝ በቦንብና በመትረየስ በእነዚህ ሀገርና ትውልድ አጥፊዎች ጊዜ ደግሞ ከዘር ማጥፋት፣መሬቱን አሳልፎ ለባእድ ሀገር ለሱዳን መስጠትና ለም መሬትና ርካሽ ጉልበት ለማግኘት ክልላችን በትግራይ ቅኝ እየተገዛ ነው ይህን ግፍ በመቃወምና በመቃወም
ወገናችን ነፍጥ ካናሳ ቆይቶል ይህን ሁላችን ስናበረታታና ስናግዝ ነበርን ግፍና በደል ባለበት ቦታ ሁሉ እምቢተኛነት፣ ትግልና አመፅ
አለና ወገኖቻችን በዚህ ደረጃ የሚደርጉት መፋለም የሚኮራ ነው። ነገር ግን ይህን የህዝባችንን አመፅና ትግል በፈጠራና ሆን ብሎ በተጭበረበረ ወሪ ወገናችን የሚደርገውን ተጋድሎ መነሻው ኤርትራ ከሆነ ከግንቦት ሰባት ጋር አያያዘውታል ። ዓላማውና ግቡ ሁለት ነው አንደኛ ህዝባችን ለመብቱ ና ነፃነቱ የሚደርጋውን ተጋድሎ በቦታው የለሉ የግንቦት ሰባት አርበኛ ባዮች እነርሱ እንዳደረጉት በማስመሰል ለአለም በዜና በማቅራብ ለህዝባችንና ለእኛ ያላቸውን ንቀት አሳይተንዋል።ስለዚህ ልሣንና ድምፅ ልንሆናው ስለሚገባ በአስቸኮይ ለዚህ ድፍራታቸው ማህበሩ መግላጫ እንዲወጣ።
ሁለተኛው ህዝባችን የሚደርገው አመፅና ነፍጥ በራሱ ሰዐትና ጊዜ በሚፈልገው ቦታ፣ ግዜና ሁኔታ የሚደረገው እንጅ በዓላም አቀፍ
ማህብረተሰብ፣ በተባበሩት መንግሥታት፣ በአውሮፓ ዩኒያን በሴቴት ዲፓርትመንትና በአፍሪካ ዩኒየን ጭምር የተወገዘ በሽብርተኛነት የተፈረጀ በራሱ ህዝብ ከተወገዘ የሽብርተኞች የነ አልካይዳ ማሰልጠኛ ተብሎ ከተፈረጀ ሀገርና መንግሥት ጋር ለአካባቢው ተወላጅ ሕዝብ ኃላፊነት የማይሰማቸው ኃይሎች ሻቢያና ግንቦት ሰባት ደባና ፕሮጋንዳ እየሰሩበት ነው ።ስለዚህ ይህ ወገናችን ነገ ሽብርተኛ ተብሎ በአይሮፕላን ቦንብና መርዝ እንደ ሱማሌና የመን
እንዲደበደብ የሚስደርግ ሥራ እየተሰራ ስላሆነ ይህን ህዝብና ኢትዬጵያውያን የማያውቁት በደል መግላጫ በማውጣት ለህዝባችሁ
ድምፅ እንድትሆኑ። በዚህ አጋጣሚ ጥሪ አደርጋለሁ።
ኢትዬጵያ ለዘላለም ትኑር።